# አሲምባ ርዕሰ አንቀጽ

Editor's Note ቁጥር 1/2012

# አገር የማዳን ጥሪ!!

ዛሬ ዋልታ ረገጥ በሆኑ ዘረኞችና የሃይማኖት ጽንፈኞች የተፈጠረው የውስጥ ግጭት አገራችን ኢትዮጵያን ፈተና ላይ እንደጣላት የማያውቅ ዜጋ አለ ብሎ ማመን ያስቸግራል። አዎን ይህ ዋልታ ረገጥ በሆኑ ዘረኞች ውስጥ ያለው የሥልጣን ሽኩቻና የውስጥ መናቆር ለራሳቸው መዳከምና የክልል ሥርዓታቸውም ለመበስበሱ አመላካች ቢሆንም፤ የመጨረሻ ዕስትንፋሳቸው ከመጥፋቱ በፊት የጋራ ጠላት በጋራ በሚል ፈሊጥ አማራን እንደ ብሄር፣ ተዋህዶን እንደሃይማኖትና አማኞችን በሙሉ፤ ከራሳቸው የተለየውን ዘር እንደ ሕዝብ ይዘው ለመጥፋት ወሳኝ ፍልሚያ ላይ የሚገኙ ይመስላል። ታዲያ ይህን እኩይ ተልዕኳቸውን ማክሸፍ ደግሞ የሁሉም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ታሪካዊና ብሄራዊ ግዴታ ነው። ይህም አጥፍቶ መጥፋት የሚለው የትግራይና የኦሮሞ ጽንፈኞች የጋር ፍልስፍና ነው። በአገር ላይ የመጣ እርግማን እንደመሆኑም መጠን በሁሉም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን መወገዝ ያለበት የሙት መንፈስም ነው ። አዎን ቁሮም ግፍ የወለደው ግፈኛ መንጋ መሆኑ እንዳለ ሁኖ፣ ጽንፈኛ የሆነው የኦነግ ፖለቲካና ጎሳ ተኮር የሆነው የወያኔ የክልል ሥርዓት ውጤት መሆኑ ግን መታወቅ አለበት። በወያኔዎችና በሻቢያ ቀጭን ትዛዝ የሚዘወረው ኦነግና ጠባብ ብሄርተኞች ባጠቃላይ በ1960ቹ በኢትዮጵያ ተማሪዎች የተጠየቁትን የፍትህ ጥያቄዎችን አጣመው አገራችን ኢትዮጵያን ለማፍረስ ተግተው የሠሩበት አጥፍቶ መጥፋት የሚለው የጋራ ፍልስፍናቸው ውጤት መሆኑን ልንገነዘበው ይገባል።

ያኔ በተማሪዎቹና በተራማጅ ምሁራን የተጠየቁት ጥያቄዎች ሕዝባዊና አገራዊ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ለሁሉም የሥርዓት ለውጥ እንጅ አገር የማፍረስም ሆነ ሕዝብ በሕዝብ ላይ የማነሳሳት ቁርሾ ለመፍጠር አልነበረም። ተራማጅ ምሁራን ና ተማሪው ካነሷቸው ጥያቄዎች ዋና ዋናዎቹን ለምሳሌ "መሬት ላራሹ"፣ "የብሄሮች ዕኩልነት"፣ "የሃይማኖት ዕኩልነትና" "ሕ ዝባዊ መንግሥት ይቋቋም" የሚሉ ነበሩበት። በተቃራኒው ጠባብ ብሄርተኞችና ተገንጣዮች ግን አገራችንን ለማፍረስ ተግተ ው የሠሩት እነኝህ መሠረታዊ ጥያቄዎች ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በሚለው ማዕቀፍ ውስጥ እንዳይፈቱ ማኮላሸት ነበር። ሁኔታውን አዛብተው ከሥርዓት ለውጥ ይልቅ የኢትዮጵያዊነት መሠረቶች ናቸው ብለው ባነጣጠሩባቸውና በጋራ

የሚጠሏቸው ጎሳና ሃይማኖት እንዲሁም የፖለቲካ ስብስቦችና አስተሳሰቦች ላይ የማያባራ ማደናቆሪያ ዘመቻዎች አደረጉ። ለዚያም ነው በአማራ፣ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ በጋራ ታሪካችንና በኢትዮጵያ የግዛት አንድነት ላይ የሚዘምቱት። ለአለፉት 40 አመታትና ከዚያም በላይ የዘለቀው የጸረ ኢትዮጵያነት ትግላቸውና የዘሩት የዘረኝነት መርዝ ዛሬ ፍሬ አፍርቶ ያገኘውን እየበላ፣ ያየውን ሁሉ የሚገልና የሚያቃጥል፣ አስከሬን የሚጎትትና ሰውን ዘቅዝቆ የሚሰቅል ቄሮ የሚባል አውሬ አፍ ርቶ ቁጭ ያለው። **የሚገርመው ዛሬ ለኦሮሞ ሕዝብ ነጻነት እንታገላለን የሚሉን ቢያንስ ላለፉት 30 ዓመታት ያስተዳደሯቸውና በደል የፈጸሙባቸው የበሰበሰው የክልላቸው ሥርዓት ቁንጮዎች ኦሮሞዎች ሆነው እያለና የአጼው ሥርዓትም እንኳን የአማራ መንግሥት ነበረ ብንል፣ ያ ሥርዓት ከወደቀ ከ45 ዓመት በላይ በኋላ ዛሬም ተነሥተው አማራዎች እንደሚበድሏቸው ሁሉ ከክልላችን ይውጡ በሚል ፈሊጥ በተደጋጋሚ እንዳደረጉት ሁሉ ዛሬም የሚፈጽሙት የወገን ጭፍጨፋ ሊወገዝ የሚገባው ነው።** ይህ ዕብደት ደግሞ ዛሬ እንኳን ታሠሩልን የምንላቸው ሥራዓቱ የወለዳቸው ግልገሎች እነ ጃውር ብቻቸውን የፈጠሩት ሳይሆን ዋና መሠረታቸው አሁንም ተንሠራፍቶ ያለው የዘረኞቹ የክልል ሥርዓት መሆኑን የዘነጋንና ተወደደም ተጠላ ባለማወቅም ይሁን፣ በሥንፍና ወይ ለራሥ ጥቅም፤ ኢትዮጵያዊነትን ከኮረኔሉ ጫማ ወድቀን እናገኛለን ብለን የሞቀውን ፀረ ዘረኘነት ፖለቲካ ትግል ያቀዘቀዝነውም ብንሆን ከተጠያቂነት አናመልጥም። ማለትም ኮሎኔል ዓብይ ባለው በዘረኛው ሥርዓት ጥርሱን ንቅሎ ያደገና ዛሬ በለሥ ቀንቶት በሥርዓቱ ተመርጦ (የኢቲዮጵያ ሕዝብ አልመረጠውም)፣ ባለው የዘረኞች ሥርዓት ሕገ መንግሥት ሀገሪቱን እያስተዳደረትና ከላይ ከርዕሰ ብሔርነት እስከ ቀበሌ ድረስ የሚገዙን በቦታቸው ተቀምጠው ያሉ ዘረኞች ሆነው አዲስ ለውጥ መጥቶልናል ብሎ መዘናጋት አደጋው ከፍተኛ መሆኑን ይኸው የቄሮ አጸያፊ ተግባር በማያወላዳ መልኩ ሊያስተምረን ይገባል። ሹሙ በሥልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ በያካባቢው ሕዝብ ሲጨፈጨፍና ሀገር ሲነድ፣ የአማራ ሴት ለጆች ከኦሮሞ ዩኒቨርሲቲ ደብዛቸው ሲጠፉና የመሳሰሉት ወንጀሎች ሲፈጸሙ የየክልሉ መንግሥታት፣ ፖሊሲች፣ ልዩ ኃይሎች፣ የፌዴራሉ ጦርና የስለላ መረቡ ከቅርብ እርቀት ሆነው መመልከታቸው ለምን ይሆን? ብለን መጠየቁም ተገቢ ነው። አብረን ልንመረምረውም ይገባል።

ታዲያ የዕለቱ አንገብጋቢ ጥያቄ መሆን ያለበት ይህን አደጋ ለመቀልበስስ ምን መደረግ አለበት? የሚለው መሆን አለበት ። ልብ ያለው ልብ ይበል! ጆሮ ያለውም አጥርቶ ይስማ! አንገትም የተሠራው አዙሮ ለማየት ነውና መጀመሪያ አገራችንን ለማዳንና ሕዝባችንን ለመታደግ ህሊና ይኑረን እንላለን። ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ የኔ ነው የምትለው መንግሥት

# አሲምባ ርዕሰ አንቀጽ

Editor’s Note ቁጥር 1/2012

የላትም። ራሱን መንግሥት ነኝ ብሎ በሚጠራው የዘረኞች ስብስብና ሹሙ ሥር የተደራጀው መከላከያ ኃይል፣ የፌደራል ፖሊስና የሥለላ መረብ፣ የየክልሉ ፖሊስና ልዩ ኃይል በሙሉ ጠባብ ብሄረተኞች ከአዘጋጁት ነብሰ-ገዳይ ቄሮ ጋር ላለመመሳጠራቸው ምን ማስተማመኛ አለን? በአማራና በኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አማኞችና ቀሳውስቶች እንዲሁም የኛ ዘሮች አይደላችሁም በሚል በተደጋጋሚ የሚደረገው የዘር ማጥፋትና ማፈናቀል የግድያ ዘመቻ፤ በየጊዜው የሚነሱ ያካባቢ ጥያቄዎችን ታከው ብቅ ብለው ጉዳት የሚያደርሱሱትስ መሠረታዊ ችግሩ ከየት ላይ ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ይኖርብናል። ሕዝቡ ራሱን አደራጅቶ፣ ራሱን መከላከልም ይችል ዘንድ አገር ወዳድ ሁሉ የሚችለውን ሁሉ ማድረግ ያለበት ነገ ሳይሆን ዛሬ ነው።

ሌላው ምጸት ደግሞ ለውጥ መጣልን፣ አብይን እንደግፍ በማለት ዜጎችን ለማዘናጋት የሚከጅሉ ወገኖች መኖራቸው ነው። ለአለፉት 28 ዓመታት ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የጫነው ሥርዓት፣ የገነባው ተቋም፣ ያበጀው የጎሳ ፖለቲካና የቀረጸው የከፋፍለህ ግዛ ሰነድ ሳይቀደደና በአዲስ ሳይለወጥ ለውጥ አለ ብሎ ማናፋትና መቀበል እብደት ነው ብለን እንነግራቸዋለን። <u>አሁንም አገራችን ውስጥ ፍትህ ሊመጣ የሚችለው ሕዝብ ራሱ መርጦ በሚሾማቸው ግለሰቦች ሲስተዳደርና ሳይፈልጋቸው ሲቀር ደግም ሹም ሽር የማድረግ ልዕለ-ሥልጣኑ የተረጋገጠበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲኖር ብቻ ነው።</u> ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም እንዲሉ የግለሰቦች መቀያየር፣ የባለሥልጣናት ቦታ መለዋወጥና የእርስ በእርስ ሹምሽር መደራረግ ለሕዝቡ ሊያመጣ የሚችል ፋይዳ በጭራሽ የለም ነው ቁምነገሩ። የሕዝብን ሁለገብ ጥያቄ መመለስ ቀርቶ በሙስናና ተመሳሳይ ወንጀል በመፈጸማቸው መጠየቅ ያለባቸው ባለሥልጣናት እንኳ እንዳሉ በአሉበት እዲባልጉና በሥልጣን እንዲቀጥሉ ነው የተደረገው። የየክልሉ ባለጌ ባለሥልጣናት ለዘረፉትና ላደረሱት በደል ሕዝቡ ሲነሳሳባቸው እጣታቸውን የሚቀሥሩት በፈረደባቸው በክልሉ በሚኖሮ ውሁዳን ሌላ ዘሮች ወይም አማሮች ላይ ሆኖ እያለ ዛሬ ተነስተን ወንጀለኞቹ እነጃዋር ብቻ ናቸው ማለት ያስቸግራል። የአረጀ ያፈጀው የዘረኞቹ የክልል ሥርዓት በአዲስና ሕዝባዊ ሥርዓት ሳይተካና በተጨባጭ በአገሪቱ ውስጥ ያሉ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ተቋማት እንደ አዲስ ሳይዋቀሩና ለሕዝብ አገልግሎት መዋላቸው ሳይረጋገጥ ለውጥ አለ ማለት ሞኝነት ነው። በተቃራኔው ለአለፉት 28 አመታት የነበረው የወያኔ/ኢ ህ አ ደ ግ ሥርዓት እንዳለ ነው የቀጠለው። ለምሳሌ፡-

- አንደኛ ወያኔ/ኢ ሕ አ ደግ ስሙን ቀይሮ ብልጽግና ፓርቲ ከመባሉ ባሻገር የይዘት ለውጥ እንኳን ያላደረገ መሆኑ፤
- ሁለተኛ የወያኔ መከላከያ ሠራዊት፣ የስለላው መረብና የፍትህ ተቋሙ በሙሉ ዛሬም እያገለገለ ያለው ተመሳሳይ ሥርዓትና ባለሥልጣኖችን መሆኑ፤
- ሦስተኛ፣ የወያኔ/ኢ ሕ አ ደ ግ ሕግና የክልል ፌደሬሽን እንደ ሥርዓት መቀጠላቸውና በወያኔ/ኢ ሕ አ ደ ግ የተመረጠው ጠ/ሚኒስተርና በሥሩ የተቋቋሙት የሥራ አስፈጻሚው የመንግሥት አካልና ሸንጎው እንደ ሥራዓቱ ቁኝጮ መቀጠላቸው ነው።

ስለዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ተቋማት እስከ ቀጠሉና በተጠያቂነት እስካልተጠቁና ብሎም የሚወገዱበት ሁኔታ እስከ አልመጣ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ አለ ብሎ ማመን ሞኝነት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ መጣ ለማለት ከላይ የተዘረዘሩት የጎሳ ላዕላይና ታዕታይ ተቋማት በሙሉ ብሄራዊና አገራዊ በሆኑ መዋቅርና ተቋማት መተካት አለባቸው ማለት ነው። ያኔና ያኔ ብቻ ነው የጎሳ ፖለቲካ ደብዛው ጠፍቶ በምትኩ በአዲስና ብሄራዊ መንግሥት ተተካ ማለት የሚቻለው።

በመጨረሻም የአብይ አገዛዝም ሆነ የቄሮ ዘመቻ በ1960ቹ ከተነሱት መሠረታዊና ሕዝባዊ ጥያቄዎች ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸው መሆኑ መታወቅ አለበት። ንጉሡን በመንግሥቱ፣ መንግሥቱን በመለስ ዜናዊ ከዚያም መለስን በአብይ መተካቱ ለሕዝቡ መሬት ላይ ጠብ የሚል መፍትሄ አለማምጣቱን የኢተዮጵያ ሕዝብ ግጥም አድርጎ የሚያውቀው ሃቅ ነው። ይባስ ብለውም ጽንፈኛው ኦነግም ሆነ ወፍ ዘራሹ ቄሮ የኦሮምን ሕዝብ ጥያቄ ጽልመት አልብሰው ትልቁን የኦሮሞ ሕዝብ አስ ከሬን ቆጣሪና የሰው ደም ያሡከረው አውሬ አስመሥለው ለመሳል የሚሞክሩት አረመኔያዊ ድርጊታቸው ሁሉ መወገዝ አለበት ። ያ ትውልድ በተለይም በኢ ሕ አ ፓ ጥላ ሥር የተሰባሰበው ወገን የብሄሮችን ዕኩልነት መሠረት ያደረገ አንድነት አለ እንጂ አምባገነኖች በየተራ ከእየጎሣው እየመጡ በፈረቃ ይግዙን አላለም። እናም በ1966 ለፈነዳው አብዮት ምክንያት የሆኑት መሬት ላራሹ፣ የብሄሮች ዕኩልነት ይረጋገጥ፣ የሃይማኖት ዕኩልነትና የድሃ ልጅ ይማር የሚሉት መሠረታዊ ጥያቄዎች እስካል ተመለሱ ድረስ የገዥዎች መፈራረቅ ብቻውን መሠረታዊ ለውጥ አያመጣም። ሩቅ ሳንሄድ የዛሬዪቱን ኤርትራን ረግጠው

የሚገዟትንና በሀገራችንም ቢሆን በየክልሉ በሕዝቡ ላይ በነቂስ የሚደርሰውን ሰቆቃ መመልከቱ በቂ ማስርጃ ነው። ስለዚህ መፍትሄው :-

- አንደኛ፡ የአንድነት ኃይሉ በነቂስ ወጥቶ ኃይሉን አጠናክሮና ሥምሪቱን አሳምሮ ኢትዮጵያ ብሎ መደራጀት አለበት፤
- ሁለተኛ፡ ሕዝቡ በተለይም ምሁሩና የፖለቲካ ድርጅቶችና የሙያና ሲቪል ተቋማት ሁሉ ዋና ዋና በሆኑ ሕዝባዊና ብሄራዊ ጉዳዮች ላይ ማተኮርና ጥቃቅን ልዩነቶቻቸውን ወደ ጎን ትተው አገር ማዳን በሚለው መሪ ቃል መሰባሰብና መታገል ይኖርባቸዋል።
- ሦሥተኛ፡ አገራችን ውስጥ ያለውን ውስብስብ ችግር አንድ ሰው ወይንም አንድ ድርጅት ወይንም አንድ ጎሳ በብቸኝነት ሊፈታው ስለማይችል ሁሉም ዜጋ በተለይም ሰፊው ሕዝብና የአንድነት ኃይሉ የሚሳተፉበት የፖለቲካ መድረክና የትግል ሂደት መኖሩ የግድ ነው።

የሽግግር መንግሥት ሲባል ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል የሚሳትፍበት የሽግግር ሂድትና ብሔራዊ መግባባትን ፈጥሮ ለቋሚ አዲስ ዴሞክራሳዊ መንግሥት በር ከፍቶ የሚያበቃ የሽግግር ሂደት ማለት ነው። አንዴ የሽግግር መንግሥት አያስፈልግም፤ ሌላ ጊዜ ምርጫ፤ አሁን ደግሞ ሲጨንቃቸው አዲሱ ሹም ያሸጋግረን ለሚሉ የሃሳብ ድሃዎችና ሠነፎች ምሁራን ያለን መልስ መሆን ያለበት ሚናችሁን ለዩ ነው። ዛሬ የሽግግር መንግሥት የሚጠይቁ ሰዎች ለሥልጣን ሽሚያ የሚቋምጡ ናቸው ለሚሉ ጎደሎ ምሁራንም ያለን መልስ የሽግግር መንግሥት የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ አልገባችሁም ነው።

ነገሮችን ለማምታት ሲሉ ጎዶሎ ኩባያ፣ ሙሉ ኩባያ በሚል ፈሊጥ እንቶኝ እንካ ለሚሉት ሥራ ፈት ምሁራን ያለን መልስ ጸጉር ስንጠቃ ቤት አይሠራም ነው። በምርጫ ስም ሕዝቡን እያዘናጉ ወደ አልሆነ አቅጣጫ እየዘወሩ ያሉትን አድርባይ ፖለቲከኞችን አስመልክቶ ደግሞ፣ ሳንታክት የታሪክ ቀበኞች መሆናቸውን፣ የድል አጥቢያ አርበኛና ወረተኛ የፖለቲካ ነጋዴዎ ች መሆናቸውን በሚገባ ማጋለጥ ነው። የቆሙትም ለራሳቸው ከርስ፣ ወንበርና ደመወዝ እንጂ ለሀገር ንጻነትና ለሕዝብ ዕኩልነት እንዳልሆነ በግላጭ እናጋልጣቸው።

# አሲምባ ርዕሰ አንቀጽ

Editor's Note ቁጥር 1/2012

**ለማጠቃለል፡**

የሽግግር መንግሥት ሥልጣን ለመያዝ ሳይሆን ቋሚ መንግሥትና ዴሞክራሳዊ ተቋማትን ሁሉ አቋቁሞ ቦታውን ለቆ የሚያበቃ ሂደት መሆኑን መገንዘቡና ማስገንዘቡ የግድ ነውና መቀስቀሱን እንቀጥልበታለን ማለት ነው። ሁሉም የሕብረተሠብ ክፍል የሚወከልበት ማለትም በአገሪቱ ውስጥ ያሉ የሲቪል፣ የሙያና የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦችና የ ሕግ ባለሙያዎችን ያጠቃለለና ሰፋ ያለ የሽግግር ሂደት ያስፈልጋል ሲባልም ለአምባ ገነኖች የማያመች ሕዘባዊና አገራዊ መንግሥት ይቋቋም ማለት ነው።

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያቸንፋል

የአሲምባ ድረ ገጽ ዝግጅት ክፍል

ሐምሌ 23 ቀን 2012